ትምህርት ትምህርት ትምህርት ለዕኩልነት ለፍትህ ለዲሞክራሲ
ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም በዕኩልነት

# በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባባሪ ኮሚቴ
## Coordinating Committee of Exiled Members of Ethiopian Teachers' Association

*የተሰጠ መግለጫ*

*መጋቢት 8 ቀን 2009 ዓ.ም*

***የመምህራን ጩኸት -እንደመምህርት መሰሉ መንጋው ላለምት፤ ትግሉ ተፋፍሞ ይቀጥል።***

*በቅርቡ በአጠቃላይ ለመንግስት ሠራተኞች የተደረገው የደመወዝ ጭማሪ መምህራንን ባለማካተቱ በመምህራን ዘንድ ከፍተኛ ቅሬታን አስከትሏል።መምህራን ቅሬታቸውንና ጥያቄያቸውን ፒቲሽን በመፈራረም ለሚመለከታቸው ባለሥልጣናት አቅርበዋል። ነገር ግን ምላሽ አላገኙም። በመሆኑም በወሎ ፣ በጎጃምና በጎንደር የተለያዩ ቦታዎች የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ከየካቲት 2009ዓ.ም ወር መጨራሻ ጀምሮ የሥራ ማቆም አድማ በማድረግ ላይ ይገኛሉ ።ለምሳሌ በሰሜን ወሎ በዋድላ፣ በመቂት፣ በሀሙሲት፣በሰንቃ፣ በሰሪንቃ፣በመርሳ፣ በጎባላፍቶ፣ በደቡብ ወሎ በመከነሰላም፣በሳይንት፣በወልዲያ፣ በጀማና በድላንታ ወረዳዎች የሥራ ማቆም አድማዎች ተካሄደዋል። በሌሎች ቦታዎችም የስራ ማቆም አድማውን ለመቀላቀል ዝግጅቶች እየተካሄዱ ናቸው። ይህን የመምህራን የስራ ማቆም አድማ ለመቀልበስ የወያኔ አምባገነነዊ መንግስት የተለያዩ ሕገወጥ አርምጃዎችን ለመፈጸም ጥረት ማድረጉ የሚጠበቅ ስለሆነ መምህራን መብታቸውን ለማስከበር ቆርጠው መታገል ይጠበቅባቸዋል። የመምህራንና የሌሎች ሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ መብታቸው በዓለም ሠራተኞች ማህበር ( ILO= International Labor Organization) ሕግ የተደነጋገ ነው። ስራ ማቆም ዲሞክራሲያዊ መብት ነው። በአገሪቱ በሁሉም ቦታዎች የሚገኙ መምህራን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸውንና የአካዳሚክ ነጻነታቸውን ለማስከበር የሥራ ማቆም አድማን በጋራ ተግባር ላይ ማዋል የሚገባቸው ወሳኝ አርምጃ ነው።ይህ እርምጃ የወያኔን አከርካሪ ሰባሪ ነው። በርትተን መስራት አለብን።*

*በመተባበር የጋራ እርምጃ ባለመውሰዳችን በመጋቢት ወር በ2004 ዓ.ም በአዲስ አበባ ውስጥ ያሉ 50 ት/ቤቶችንና በሰሜኑ የአገራችን ክፍል በጎንዳር የተወሰኑ ት/ቤቶችን አዳርሶ የነበረው የመምህራን የሥራ ማቆም አድማ የታለመበትን ግብ ሊመታ አልቻለም ነበር። ያ በመሆኑ የተወሰኑ መምህራን የወያኔ የጥቃት ሰለባ ሆነዋል።*

*በአገራችን የትግል ታሪክ ውስጥ ትልቁን ድርሻ ይዞት ያለው የየካቲት 11 ቀን 1966ዓ,ም ሰላማዊ ሰልፍና ትግል ሁሉንም መምህራን ማሳተፍ በመቻሉ፣ ተማሪዎችም ከጎናቸው መቆም በመቻላቸው፣ የታክሲ ነጂዎችና፣ ሌሎች የሕብረሰብ ክፍሎች የመምህራንን የደመወዝ ጭማሪ ጥያቄ፣ የደሃ ልጅ ይማር ፤ ሴክተር ሪቪውን እንቃወማለን፣ ...ወዘተ ጥያቄዎቹን በመደገፍና የራሳቸውን የመብት ጥያቄዎችን በመያዝ መተባበር በመቻላቸው በወቅቱ የነበረውን ባላባታዊ ሥርዓት ከሥልጣን እንዲወርድ ከፍተኛ አተዋጽኦ አበርክተዋል። ዛሬም የሚያስፈልገን የዚያ ዓይነት የተባበረ አገርአቀፍ የሕዝብ ትግል ነው።*

*ባሁኑ ወቅት በሰሜኑ የአገራችን ክፍል እየተካሄደ ያለው የመምህራን የስራ ማቆም አድማና ትግል ተፋፍሞ እንዲቀጥል በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች ያሉ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ወላጆች፣ ሠራተኞች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ ወታደሮች፣ ባጠቃላይ ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል እንዲደግፍ አብሮም እንዲታገል በሰደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አባላት አስተባበሪ ኮሚቴ ጥሪውን ያቀርባል።*

*መብታቸውን ለማስከበር የስራ ማቆም አድማ ላይ ተሳታፊ ከነበሩት መምህራን ውስጥ 76ቱን ወያኔ አስሯል።ለምሳሌም ያህል በዋድላ ወረዳ ከባኮን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 26 መምህራን መታሰራቸው ታዉቋል። ከእነዚህ ውስጥ መ/ር ወንድወሰን ድምሴ፣ መ/ር አህመድ ኑር፣መ/ር ሚኪያስ ካሳ፣መ/ር ሲሳይ አስፋውና መ/ር በአምነት በለጠ ይገኙበታል። የመምህራኑ ቤተሰቦች በችግር ላይ የወደቁ በመሆናቸው በውጭ የሚገኙ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በሁሉም መልኩ አርዳታ በማድረግ እንዲተባበሩ አስተባባሪ ኮሚቴ ጥሪ ያደርጋል። ለወገን ደራሽ ወገን ነውና።*

P.O.Box 16632 Saint Paul, MN 55116 • Tel.: 403-402-0334 • Email: eta1941@yahoo.com

*የእኛ ሙሽራ ሹራብ ስሪ ፣ ወሰዳት አስተማሪ ተብሎ እንዳልተዘፈነ በወያኔ ስርዓት የመምህራን የኑሮ ደረጃ ምን ያህል የከፋና አስዛኝ እንደሆነ ሰሞኑን የተከሰተው ሁኔታ በቂ ማስረጃ ነው። በአዲስ አበባ በኮልፌ ቀራኒዮ በተለምዶ ቆሼ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ መጋቢት 1 ቀን 2009 ዓ.ም ከምሽቱ 2 ሰዓት ገደማ የቆሻሻ ክምር ተንዶ በመኖሪያ ቤቶች ላይ በመደርመሱ ምክንያት ቁጥራቸው ከ132 በላይ የሆኑ ዜጎቻችን እንደሞቱ የተለያዩ የዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙኃን ዘግበውታል።*
*ከሞቱት መኸል የብሩህ ተስፋ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት አስተማሪ መምህርት መሰሉ መንጋው፣ ባላቤቷና ሶስት ልጆቿዋ ሕይወታቸው አልፏል። ለመምህርት መሰሉ መንጋው፣ ለቤተሰቦችዋ፣ እንዲሁም በዚህ አስቃቂ ሁኔታ ለሞቱት ወገኖቻችን በሙሉ በስደት የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር አስተባበሪ ኮሚቴ የተሰማውን ጥልቅ ሀዘን ይገልጻል። ለቤተሰቦቻቸውም እግዚአብሔር ጽናቱን እንዲሰጣቸው ይመኛል።*

*እነዚህ ወገኖቻችን ቆሻሻ አካባቢ ኖረው፣ ቆሻሻ ተመግበው፣ ቆሻሻ ተንዶባቸው ላንዴና ለመጨረሻ አሸልበዋል። ባንጻሩ ትናንት በባዶ እጅ ወደ አዲስ አበባና የተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የገቡት የወያኔ ባለሥልጣናት ዛሬ ቢሊንየርና የባለብዙ ፎቆች ባላቤት ሆነዋል።*

*ከወር በፊት ዘረኛው የወያኔ መንግሥት ለአዲስ አበባ መምህራን የኮንዶሚኒየም ቤቶች በዕጣ ተሰጣቸው ማለቱ የሚታወስ ነው ። ቤቶቹ የተሰጣቸው ለሥርዓቱ አገልጋዮች እንጂ እንደ መምህርት መሰሉ መንጋው በችግር አረንቋ ውስጥ ለሚገኙ እንዳልሆነ ማስረጃ ፍለጋ መዳዝ አያስፈልግም። የመምህርት መሰሉ በቂ ነው።*
*የመምህራን ጩኻት መሰረታዊ የመብት ጥያቄ ነው። ከከፋ ኑሮ ለመላቀቅ ነው እንጂ እንደወያኔ መሪዎች የቅንጦት ኑሮ ለመመኘት አይደለም። ባጠቃላይ የመምህራንም ሆነ የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮ የሚሻሻለው፣ፍትሕና-ርትሕ የሚሰፍነው፣ የሕግ የበላይነት እውን የሚሆነው፣ ---ወዘተ የወያኔ ሥርዓት ሲወገድ ብቻ ነው። ለዚህም ቆርጠን እንታገል።*

*መብታችንን ለማስከበር ተባብረን እንታገል!!*
*የአስቸኳይ ጊዜ አውጁ የሕዝብን ትግል አይገታም!!*